# <u>ስተው ከሚያሳስቱ ምሁራን እንጠንቀቅ!</u>

## ሰለሞን ሽፈራው 10-06-17

ሳምንታዊው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ባለፈው ቅዳሜ መስከረም 20 ቀን 2010 ዓ.ም በወጣው የቅጽ 16 ቁጥር 924 እትሙ ላይ "የባህልና ትውፊት ተቋምን ያገለለው፣ የህዳሴ ፕሮጀክት" የሚል ፅሑፍ ይዞ ስለመውጣቱ ማስታወስ ይቻላል፡፡ ጋዜጣው "ህብረተሰብ" በሚለው አምዱ ላይ ያወጣውን ተጠቃሹን ፅሑፍ ያቀረቡትም ደግሞ ብሩህ ዓለምነህ የተባሉ ሰው ናቸው፡፡ እኚህ ፀሐፊ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህር እንደሆኑም ከስማቸው ቀጥሎ የሰፈረው ማስታወሻ ያመለክታል፡፡

እንግዲያውስ እኔም ስተው ከሚያስቱ ምሁራን እንድንጠነቀቅ በሚያሳስብ ርዕስ እቺን መጣጥፍ ለማቅረብ የተገፋፋሁት ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ይልቅስ አቶ ብሩህ ዓለምነህ ከላይ በተጠቀሰው ርዕስ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ያስነበቡን ሰሞነኛ ጽሑፍ ከአንድ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና አስተማሪ ነኝ ከሚል ግለሰብ የማይጠበቅ አጉል ድፍረትን የተላበሰ ሆኖ ስለተሰማኝ ነው፡፡ ስለዚህም አሁን በቀጥታ ወደ ዋናው የመጣጥፌ ማጠንጠኛ ነጥብ ልለፍና ከፀሐፊው ሃሳብ ጋር ያልተስማማሁበትን መሰረታዊ ምክንያት ግልጽ ለማድረግ ልሞክር፡፡

አቶ ብሩህ ዓለምነህ፣ ቅዳሜ መስከረም 20 ቀን 2010 ዓ.ም "የባህልና የትውፊት ተቋምን ያገለለው የህዳሴ ፕሮጀክት" በሚል ርዕስ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ያቀረቡትን ሰሞነኛ ጽሑፍ ጨምሮ፣ ሌሎችም መሰል ይዘት ያላቸው መጣጥፎችን ባሳለፍነው ዓመት እንዳስነበቡን ማስታወስ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ እናም ፀሐፊው የሀገራችን ህዝቦች የዘመናት አንገብጋቢ አጀንዳ እንደሆነ ባለው ኢትዮጵያን ወደ ቀደመው ከፍታዋ የመመለስ ጥረት ዙሪያ ለውይይት የሚጋብዝ ርዕሰ ጉዳይ እያነሱ የራሳቸውን እይታ የሚያንፀባርቅ ነፃ ሃሳብ መሰንዘራቸው በራሱ የሚደገፍ እንጂ የሚነቀፍ አይደለም ማለት ይቻላል፡፡ ይህ የግለሰቡ የማይገሰስ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ ሕገ መንግስታዊ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በእርግጥም "ስተው ከሚያሳስቱ ምሁራን

እንጠንቀቅ!" የሚያሰኝ ይዘትን በጎላና በሰላ መልኩ ሲከተሉ የሚስተዋሉበት አግባብ መታረም እንደሚኖርበት ግን ይሰማኛል፡፡

ስለሆነም፤ አቶ ብሩህ ዓለምነህ በተለይም መስከረም 20 ቀን 2010 ዓ.ም "የባህልንና የትውፊትን ተቋም ያገለገለው፤ የህዳሴ ፕሮጀክት" በሚል ርዕስ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ያቀረቡት ጽሑፍ በርካታ መታረም ያለባቸው ስህተቶችን እንደ ጠቃሚ ነገር ቆጥረን እንድንቀበላቸው ለማድረግ የተሞከረበት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ፀሐፊው በተጠቀሰው የጋዜጣ ላይ ሐተታቸው ከመቸውም ይልቅ ግልጽ ያደረጉልን ጉዳይም ደግሞ፤ በለየለት የታሪክ ሽሚያ ምክንያት የገሃዱን ዓለም ነባራዊ ጥሬ ሃቅ ሽምጥጥ አድርገው ለመካድ ከሚቃጣቸው ትምክህተኛ ምሁራን አንዱ መሆናቸውን ነው፡፡

ለዚህ አስተያየቴ የተሻለ ማሳያ ምክንያት ይሆነኛል የምለውም፤ አቶ ብሩህ ዓለምነህ ከላይ በተጠቀሰው ርዕስ ያቀረቡት መጣጥፍ ላይ በተለይም ሁለት የገሃዱን ዓለም ነባራዊና ታሪካዊ እውነታ ገድሎ ለመቅበር የተሞከረባቸው መሰረታዊ ስህተቶች ማግኘቴን ነው፡፡ የመጀመሪያው የአቶ ብሩህ ዓለምነህ መሰረታዊ ስህተት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል የምለው አደገኛ ነጥብ፤ የመላው የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ዕጣ ፈንታ የተቃና ይሆን ዘንድ እንደ ሀገር እጅ ለእጅ ተያይዘን በመነሳት ልንረባረብበት የሚገባውን የህዳሴ ጉዞ "ሊሳካ የሚችለው ፕሮጀክቱ ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሲተውላት (ሲሰጥ) ብቻ" እንደሆነ አድርገው ያቀረቡት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ኢህአዴግ የኢትዮጵያን የህዳሴ ጉዞ አጀንዳ ለማስቀጠልም ሆነ ዳር ለማድረስ የሚያስችል ተፈጥሯዊ ባህሪ የለውም ሲሉ የሰበኩበት አግባብ ነው፡፡

ስለዚህ እኔ እንደርሳቸው "በመቀሌ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና መምህር" የሚል ተቋማዊ ገጽታን ለመላበስ የሚያስችል ሽፋን ባይኖረኝም ቅሉ፤ ከላይ የተጠቆሙት ሁለት ነጥቦች ተሳስቶ የማሳሳትን ደፋር ድምዳሜ ያዘሉ ናቸውና ሊታረሙ ይገባል ስል ለመሞገት እገደዳለሁ፡፡ ምክንያቱም ደግሞ በእንደዚህ ዓይነቱ የመቶ ሚሊዮን ህዝቦችን ህብረ ብሔራዊ የጋራ ማንነት መሰረት አድርጎ መቃኘት በሚኖርበት የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ዘለቄታዊ ዕጣ ፈንታ ዙሪያ

ከሚያጠነጥን መሰረታዊ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ መልኩ የሚነሳን መሰል አስተያየት በቸልታ ማለፍ አይገባም የሚል አቋም አለኝና ነው፡፡

እናም ከዚሁ ጽኑ እምነቴ በመነሳት ወደምሰነዝረው ምክንያታዊ ትችት ከማለፌ በፊት፤ የጉዳያችን ማጠንጠኛ ነጥብ በሆነው የአቶ ብሩህ ዓለምነህ መጣጥፍ ላይ ለተስተዋለው መሰረታዊ ስህተት የተሻለ ማሳያ ይሆናሉ ካልኳቸው ሁለት የፀሐፊው ደፋር ድምዳሜዎች ጥቂት አንቀፆችን ለአብነት ያህል ቀንጭቤ በመጥቀስ ለቅሬታዬ ተጨባጭ አስረጅ አቀርባለሁ፡፡ በዚህ መሰረትም የኢትዮጵያውያን ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን የተለየ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ፈርጀ ብዙ ልዩነት ኢህአዴግ መራሹ ፌደራላዊ ስርዓት የፈጠረው ሰው ሰራሽ ችግር ለማስመሰል ሲሞክሩ ፀሐፊው አቶ ብሩህ ዓለምነህ "በኛ ሀገር ታሪክ ውስጥ ከታዩ መንግስታት ህዳሴ የሚለውን ቃል በጣም ጎላ ባለ መልኩ እየተጠቀመ ያለው ኢህአዴግ ቢሆንም፤ የፅንሰ ሃሳቡ አጠቃቀም ላይ ግን ሁለት ችግሮች አሉበት፡፡ የመጀመሪያው፤ ህዳሴ የጥንት አያቶችን ባህል ናፍቆት እንደመሆኑ መጠን የታሪክ ሽክም መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ከብሔር የታሪክ ቅራኔ ተወለድኩ የሚለው ኢህአዴግ የታሪክ ሽክም ስላለበት (እሱ ራሱ የቅራኔው አካል ስለሆነ) እዚህ የታሪክ ሽክም ላይ ቆሞ ህዳሴን ለማምጣት መሞከር ማለት ራስን እንደመቃረን ነው" ብለዋል፡፡

ፀሐፊው ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ አፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ድረስ ባለው የታሪካችን ክፍል ወደ ስልጣን የመጡት ነገስታት፤ የ"ከሸፈም" ቢሆን የህዳሴ ፕሮጀክት ነበራቸው ሲሉ በገለፁበት አንቀጽ አፄ ቴዎድሮስ፤ አፄ ሚኒሊክና አፄ ኃይለሥላሴ የየራሳቸውን ያላሰለሰ ጥረት ያደረጉ ስለመሆናቸው ጠቅሰው አፄ ዮሐንስን ግን ዘለዋቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ እርሳቸው አጥብቀው የኮነኑትን ከብሔር ቅራኔ የሚመነጭ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ባህል ወልዶ ያሳደገው ማን እንደሆነ አሳምሮ የሚያሳይ ማረጋገጫ ነው ብለን እንድናጠቃልል ያስገድዳል፡፡፡ ከአራቱ የድህረ ዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያ ነገስታት መካከል አንዳቸውም እንኳን ስልጣን ላይ በቆዩበት ጊዜ ለእነርሱ ዘውዳዊ አገዛዝ አላመች የሚል የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብት ጥያቄ ያነሱ የብሔር ብሔረሰብ ህዝቦችን በማን አለብኝነት ሲጨፈጭፉና ሲያስጨፈጭፉ የመስተዋላቸውን መራር ታሪካዊ ጥሬ ሀቅ ትንፍሽ አለማለታቸውም ብሩህ ዓለምነህን በደንብ እንድናውቃቸው ያደርጋል፡፡

ምናልባት አያውቁ ይሆን እንዴ? የሚል ተራ ቅንነት እንዳያድርብንም ደግሞ ጸሐፊው “የበቁ፤ የነቁ” የፍልስፍና ምሁር ስለመሆናቸው በአዲስ አበባ የግል ፕሬስ ሚዲያዎች ላይ ምስክርነት ይሰጣቸዋል፡፡ እስቲ አሁን “ብሩህ ዓለምነህ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህርና የኢትዮጵያ ፍልስፍና መፅሐፍ ደራሲ” እያሉ ጋዜጣ ላይ መፃፍ ምን የሚሉት ፈሊጥ ነው? እንደኔ እንደኔ ግን ግለሰቡ “በዚህን ያህል መጠን የበቃሁ፤ የነቃሁ የፍልስፍና ሊቀ ስለሆንኩ፤ ልሳሳት አልችልምና የምነግራችሁን ሁሉ ያለ አንዳች ማቅማማት ተቀበሉኝ” ለማለት የፈለጉ ይመስለኛል፡፡ ደግሞስ እርሳቸው ከኢህአዴግ የተሻለ ሀገራዊ ራዕይና ከታሪክ ባለዕዳነት የፀዳ መንግስታዊ ቁመና እንደነበራቸው አድርገው ያቀረቧቸው የድህረ ዘመነ መሳፍንት ኢትዮጵያ ነገስታት የየራሳቸውን ሸጋ ሸጋ የህዳሴ ህልሞች እያለሙ ማለፋቸው በራሱ እንደ ቁምነገር ከተቆጠረ፤ ከነገስታቱ መካከል አንዱ የነበሩት አፄ ዮሐንስ አራተኛ ስለምን ስማቸው ሳይወሳ ቀረ? እውን እራሳቸውም እንደ ህወሐት/ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ትንሳኤ ለማለም የሚያስችል የጀርባ ታሪክ ስላልነበራቸው ነውን እነ ብሩህ ዓለምነህ ከነመፈጠራቸው የማያውቁ ያህል የዘነጓቸው!?

እንደዚያ ብለን እንዳናምን ደግሞ፤ የትግራይ ተወላጁ አፄ ዮሐንስ አራተኛ የእናት ሀገራቸውን ዳር ድንበር ጥሰው ከመጡ ባዕዳውያን ወራሪዎች ጋር የሞት ሽረት ትግል ገጥመው እንደተራ ወታደር በጨበጣ ውጊያ ሲፋለሙ ለማይገሰስ ነፃነት የወደቁ ብቸኛው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ስለመሆናቸው ድፍን ዓለም የሚያውቀው እውነት ነውና ለእብለት አያመችም፡፡ እነብሩህ ዓለምነህ “መተማን በህልም” የሚለውን የሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ግጥም አላነበቡት ይሆን? እስቲ ታላቁ ባለ ቅኔያችን “እሳት ወይ አበባ” የተሰኘው ተወዳጅ የግጥም መድበሉ ላይ ካሳተማቸው በሚያስደምም ምስጢራዊነት የበለፀጉ ግጥሞቹ መካከል አንዱ የሆነውን “መተማን በህልም” የሚል ርዕስ ያለው ድንቅ ስራ አንብቡትና የኢትዮጵያን ህዳሴ ለማለም የሚያስችል ተፈጥሮ የለውም መባል የሚገባው ፖለቲከኛ ማን እንደሆነ ትረዳላችሁ፡፡

እንዲሁም ደግሞ “የባህልና የትውፊት ተቋምን ያገለለው፤ የህዳሴ ፕሮጀክት” በሚል ርዕስ ያቀረቡት ሰሞነኛ ሐተታቸው ላይ እንደ ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ ወስደው ስለፃፉበት

“ህዳሴ የጥንታዊያን አያቶችን የስልጣኔ አሻራ ከመናፈቅ በሚመነጭ የዳግም ልደት ስሜት መነሳሳትና ወደቀደመው ታላቅነት ለመመለስ የሚያስችሉ ትውፊታዊ ዕሴቶችን ማዳበር (መከለስ) ነው፡፡ ከዚህ አኳያ አገራችንን በሌላው ዓለም ህዝቦች ዘንድም ጭምር አድናቆት እንዲቸራት እያደረጉ የሚገኙት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ በዓላትና መሰል የእምነቱ ተከታዮች መንፈሳዊ መስተጋብር የሚገለፅባቸው ትውፊቶች እንደመሆናቸው መጠን፤ የህዳሴ ፕሮጀክቱ ለቤተክርስቲያኗ መተው ይኖርበታል” የሚለው መሰረተ ሃሳብ ራሱ ከአንድ የሀገሩን ነባራዊ እውነታ በቅጡ የማገናዘብ ኃላፊነት ሊሰማው ከሚችል ምሁር ዜጋ የሚጠበቅ ነውን? ማሰኘቱ አይቀርም ባይ ነኝ እኔ፡፡ በተለይም ደግሞ እርሳቸው 160 ዓመት እንዳስቆጠረ አድርገው ያቀረቡት ኢትዮጵያን ወደ ቀደመው የታላቅነት ታሪኳ የመመለስ ጥረት እስከዛሬ ድረስ ያልተሳካበት ምክንያት “የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ያገለለ ፕሮጀክት ስለነበር ነው” የሚል ድምዳሜ ላይ የደረሱበት እይታቸው በእጅጉ የተንሸዋረረ ሆኖ አግኝቸዋለሁ፡፡

በግልጽ አነጋገር፤ የድህረ ዘመነ መሳፍንቷ ኢትዮጵያ ድህነትና ኋላ ቀርነት፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣው፤ መላ የብሔር፤ ብሔረሰብ ህዝቦቿን በእኩል የሀገራዊ ፍቅር ስሜት ለልማት ሊያሰልፍ የሚችል የጋራ መግባባት ላይ መድረስ እንዳይቻል የሚያደርግ አድሎአዊ የመንግስት ፖሊሲን የሚከተሉ ጨቋኝ ስርዓቶች ስለነበሩ እንጂ፤ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን አዎንታዊ ሚና ስላልታከለበት አይደለም፡፡ ስለዚህ አሁን ላይ ሀገራችን የምትመራበት የፌደራሊዝም ስርዓት ዋነኛ ዓላማም፤ መላውን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በእኩል የሀገራዊ ፍቅር ስሜት ለጋራ እድገትና ብልጽግና ተሰልፈው ድህነትንና ኋላ ቀርነትን ድል የሚነሱበት ፈጣን የጋራ ልማት እንዲቀዳጁ ማስቻል ተደርጎ ቢወሰድ እውነታውን በተሻለ መልኩ ይገልፀዋል፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን፤ የብሔር ፖለቲካን ወልዶ በማሳደግ መከሰስም መወቀስም ያለባቸው የድህረ ዘመነ መሳፍንቷ ኢትዮጵያ ጨቋኝ ነገስታት እንጂ ኢህአዴግ ሊሆን አይችልም፡፡ ለዚህም ደግሞ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ከዛሬ 60 ዓመት በፊት “መተማን በህልም” በሚል ርዕስ ከፃፈውና የአፄ ዮሐንስን አሳዛኝ አሟሟት ከመሰጠረበት ምጡቅ ቅኔ የተሻለ ታሪካዊ አስረጂ

አይኖርም ማለት ይቻላል፡፡ ታዲያ እውነታው እንዲህ ሆኖ ሳለ፤ የብሩህ ዓለምነህ ዓይነቶቹ ጎጠኛ ምሁራን የፌስቡክ ዘመን ውዥምብር የፈጠረላቸውን ምቹ ሁኔታ እንደ መልካም አጋጣሚ ተጠቅመው የእነርሱን ጭፍን ጥላቻ ያመነቸከው ዘረኝነት ኢህአዴግ አመጣሽ ለማስመሰል ሲቃጣቸው እያየን እንዳላየን የምናልፍበት ምን ምክንያት አለ? ስለዚህም እንደኔ እምነት ከሆነ፤ ግለሰቡ ከላይ በተጠቀሰው የመስከረም 20 ቀን 2010 ዓ.ም ጽሑፋቸው "ህዳሴን ለማምጣት እንደመነሻ መወሰድ ያለባቸው የጥንት አያቶቻችን ትውፊታዊ ዕሴቶች በሙሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ በዓላትና መሰል ነገሮች ናቸው፡፡ ስለሆነም የህዳሴ ፕሮጀክቱን የማሳካት ሚና ለቤተክርስቲያኗ ሊተውላት ይገባል" ሲሉ የሰነዘሩት መሰረተ ሃሳብም ጭምር ከአንድ የሀገሩን ነባራዊ እውነታ በቅጡ ከሚገነዘብ ምሁር ዜጋ የሚጠበቅ አይደለም ብንል ተገቢነት የሚኖረው ይመስለኛል፡፡

ይህን ስልም ግን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፀሐፊው የጠቀሷቸውን ጠቃሚ የጥንታዊ ማንነታችን መገለጫ የሆኑ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ትውፊቶች ጠብቃ በማቆየት ረገድ የሀገር ባለውለታ አይደለችም ለማለት ፈልጌ እንዳይመስላችሁ፡፡ ይልቅስ እንደ ኢትዮጵያ በርካታ ሃይማኖቶች ባሉበትና ምዕመናኑ ለዘመናት ያህል ዕርስ በርስ ተከባብረው በኖሩበት ሀገር ውስጥ የህዳሴ ጉዞን ያህል የጋራ አጀንዳ ለአንደኛው እምነት ተከታዮች ብቻ መተው አለበት የሚለው የፍልስፍና መምህሩ "ምክር" ለየትኛውም ወገን የሚበጅ ድምር ውጤት ሊያመጣ ስለማይችል እንጂ፡፡ ምንም እንኳን ፍልስፍና በተሻለ መልኩ ወደ እውነት ለመቅረብ የሚረዳ የእውቀት ዘርፍ ነው ተብሎ ቢታመንም፤ አቶ ብሩህ ዓለምነህ ግን ይህን ዓለም አቀፋዊ የስምምነት ጽንሰ ኃሳብ እንድንጠራጠር የሚጋብዝ ኢ-ምክንያታዊ ድምዳሜን የመረጡ ይመስላሉ፡፡

ስለሆነም "በእንትን ዩኒቨርሲቲ፤ የእንትን መምህር" የሚለውን ፈሊጥ ተቋማዊ ገጽታ ለመላበስ ሲሞክሩበት የሚስተዋሉ የብሩህ ዓለምነህ ዓይነቶቹ ትምክህተኛ ምሁራን በተለይም ወጣት ዜጎቻችንን ለማሳሳት ያለመ አጉል ድፍረታቸውን ያቆሙ ዘንድ ልንነግራቸው ይገባል፡፡ አለበለዚያ ግን እነርሱ የየራሳቸውን የአስተሳሰብ ግዛት ለማስጠበቅ ሲሉ ብቻ፤ የዚችን ሀገር

ህዝቦች የጋራ እጣፈንታ የሚወስኑ ርዕሰ ጉዳዮችን እንዳሻቸው አድርገው እያንሸዋረሩ በመተርጎም፤ ወጣት ዜጎቻችንን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ የሚወስዱበት አግባብ ተቀባይነት እንዲኖረውና የዚያኑ ያህልም ጥረታችን ሁሉ የእንቧይ ካብ እየሆነ እንዲቀር እድል እንደመስጠት ሊቆጠር ይችላል፡፡ በተረፈ ግን እኔ ምናልባት ተሳስቼ ብገኝ ለመታረም ዝግጁ መሆኔን እየገለጽኩ ለዛሬ እዚህ ላይ አብቅቻለሁ፡፡ ***መዓ ሰላማት!***